የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ—መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 45
ADDIS ABABA–8th April, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፭/፲፱፻፺፭ ዓ·ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ መንግሥትና በቱርክ መንግሥት መካከል በጤና መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ...................................... ገጽ ፪ሺ፩፻፵፩

## CONTENTS

Proclamation No. 325/2003

Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Cooperation in the Field of Health Proclamation ...................................... Page 2141

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፭/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጤና መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በቱርክና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ወዳጅነትና ትብብርን ለማስፋፋት የሚያስችሉ መሠረታዊ ስምምነቶችን ከቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተፈረመ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ መስኮች የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ትብብርን ለማስፋፋት ያለውን ፈቃደኝነት በተደጋጋሚ የገለጸ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጤና መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወሰነ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቱርክ መንግሥት መካከል በጤና መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 325/2003

### A PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKEY ON COOPERATION IN THE FIELD OF HEALTH

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has entered into basic Agreement with the Government of the Republic of Turkey for the promotion of friendly relations and cooperations among the people of the two countries;

WHEREAS, the Government of Ethiopia has expressed its willingness to develop cooperations in various fields in conformity with mutual benefits;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Cooperation in the Field of Health at its session held on 8th day of April, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as "The Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Cooperation in the Field of Health Proclamation No. 325/2003."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱ ስለማጽደቅ</u>

መጋቢት ፬ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጤና መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በዚህ አዋጅ አጽድቋል።

፫· <u>የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይህንን ስምምነት በተግባር እንዲያውለው በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Cooperation in the Field of Health signed on 13th March 2000, is hereby ratified by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3. *Responsibility of the Ministry of Health*

The Ethiopian Ministry of Health is hereby empowered to implement this treaty.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 8th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE